Amharic

# ተጨባጭ መረጃ ቅጽ 2

# አገር አቀፍ የአካል ጉዳተኝነት የመድህን ዋስትና አሰራር ምንድነው?

**ይህ ተጨባጭ መረጃ የቀረበው ለአካል ጉዳተኞች መብት መከበር በቆመዉ እና እንዲሁም የሚያስፈልጋቸዉ መሰረታዊ ፍላጎት እንዲማላ በሚሰራ AMPARO በተባለ ድርጅት ሲሆን ከተለያየ ባህል እና ቋንቋ ለመጡ ልዩ ልዩ ማህበረሰቦች ስለአገር አቀፍ የአካል ጉዳተኝነት የመድህን ዋስትና አሰራር በቋንቋቸዉ የተተረጎመ መረጃን ለማቅረብ ነው።**

**አገር አቀፍ የአካል ጉዳተኝነት የመድህን ዋስትና አሰራር በምህፃረ ቃል** NDIS ተብሎ ሲጠራ የአካል ጉዳት ያለባቸዉ ሰዎች የሚያስፈልጋቸውን እንክብካቤና ድጋፍ እንዲያገኙ የሚረዳ አዲስ መንገድ ነው። ይህ ያለክፍያ ነጻ የሆነ አገር አቀፍ አሰራር በመላው አውስትራሊያ ላሉ ሰዎች አንድ ዓይነት ይሆናል። አገር አቀፍ የአካል ጉዳተኝነት የመድህን ዋስትና አሰራር በመላው አውስትራሊያ በፈረንጆቹ አቆጣጠር በ2019 የሚዘረጋ ሲሆን በኩዊንስላንድ የሚጀምረው በ2016 ነው። ከአገር አቀፍ የአካል ጉዳተኝነት የመድህን ዋስትና አሰራር (NDIS) እርዳታ የሚያገኙ የአካል ጉዳት ያለባቸዉ ሰዎች “ተሳታፊዎች” ተብለው ይጠራሉ።

# አገር አቀፍ የአካል ጉዳተኝነት የመድህን ዋስትና መስፈሪት

**አገር አቀፍ የአካል ጉዳተኝነት የመድህን ዋስትና አሰራር (NDIS) በአውስትራሊያ ውስጥ ለሚኖሩ** የአካል ጉዳት ላለባቸዉ ሰዎች ሆኖ

- አገር አቀፍ የአካል ጉዳተኝነት የመድህን ዋስትና አሰራርን (NDIS) መጠቀም ሲጀምሩ እድሜያቸው ከ65 ዓመት በታች ለሆናቸው
- የአውስትራሊያ ዜጋ **ወይም** ቋሚ የነዋሪነት ፈቃድ ያለው ሰው **ወይም** ልዩ የመከላከያ ቪዛ ለያዘ የኒውዚላንድ/New Zealand ዜጋ
- የአካል ጉዳተኝነቱ እስከ ‘ሂይወት መጨረሻ’ የእለት ተእለት እንቅስቃሴ ለማድረግ ችግር የሚፈጥር እና በቶሎ የማይጠፋ መሆን ናቸው።

አገር አቀፍ የአካል ጉዳተኝነት የመድህን ዋስትና አሰራር ድጋፍን ለማግኘት አስፈላጊ መስፈርት ለማያማሉ ሰዎች አገር አቀፍ የአካል ጉዳተኝነት የመድህን ዋስትና አሰራር ተስማሚ የሆኑ ድጋፎችን እንዲያገኙ ከሌሎች አገልግሎቶች ጋር ማገናኘት ይችል ይሆናል።



# ምርጫ እና መቆጣጠር

ባለፉት ጊዜያቶች በአውስትራሊያ ውስጥ ብዙ የአካል ጉዳት ያለባቸዉ ሰዎች አብዛኛውን ግዜ ከማህበርሰብ ህይወት እንደተገለሉ ይሰማቸው ነበር፤ የሚደረግላቸው ድጋፍ እንዴት መቅረብ እንደነበረበትም አነስተኛ የሆነ ምርጫ ነበራቸው። አሁን ግን በአገር አቀፍ የአካል ጉዳተኝነት የመድህን ዋስትና አሰራር (NDIS) የታቀፉ ተሳታፊዎች ምን አይነት ድጋፍ እንደሚፈልጉ እና ድጋፉን እንዴት ማግኘት እንዳለባቸው መወሰን ይችላሉ።

# ተገቢና አስፈላጊ ድጋፍ

የአካል ጉዳት ያለባቸዉ ሰዎች የህይወት ዓላማቸውንና እና ህልማቸውን እንዲያሳኩ እንዲሁም የበለጠ ራሳቸውን እንድችሉ ለማስቻል ለሚደረግ ተገቢ እና አስፈላጊ ድጋፍ አገር አቀፍ የአካል ጉዳተኝነት የመድህን ዋስትና አሰራር (NDIS) የገንዘብ ክፍያ ያደርጋል።

**የአካል ጉዳት ያለባቸዉ ሰዎች በማህበርሰባቸው ውስጥ በማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሰዎች ላይ ለመሳተፍ ሲያስፈልጋቸው አገር አቀፍ የአካል ጉዳተኝነት የመድህን ዋስትና አሰራር (NDIS) ድጋፍ ያደርግላቸዋል።** እንቅስቃሰዎቹ የሚያካትቱዋቸው፡



- ከሌሎች ሰዎች ጋር ግንኙነት መፍጠር እና ቁርኝት ማድረግ – ከቤተሰብና ከጓደኞች ጋር መሆን
- በማህበረሰብ ውስጥ በመታቀፍ የተለያዩ ማሕበራዊ እንቅስቃሴዎችን መሳተፍ - ለምሳለ የመዝናኛ እንቅስቃሴዎች
- ወደ ትምህርት ቤት መሄድ፣ ጥናትና ስልጠና ማካሄድ - እንደ ቴፍ/TAFE ወይም የዩኒቨርሲቲ ትምህርት
- አጠቃላይ የእለት ተእለት ኑሮ ሥራዎች - ውሳኔ ማድረግ፣ የፍጆታ ክፍያዎችን መፈጸም እና ችግር መፍታት
- መግባባት - የራስን ሃሳብ ለለሎች መናገር እና ሌሎችን መረዳት
- እንቅስቃሴ- በቤትና በማህበርሰብ ዉስጥ መንቀሳቀስ ወይም ይህንን ለማድረግ የሚያስችሉ መሳሪያዎችን ማግኘት
- እራስን መንከባከብ እና ልዩ የሆነ የጤና እንክብካበ ፍላጎት - ገላ ለመታጠብ፣ ልብስ ለመልበስ እና ምግብ ለመመገብ እርዳታ ማግኘት
- የቤት ውስጥ ሥራዎች- ምግብ ማዘጋጀት እና ቤት ማጽዳት
- ሥራ - ሥራ መፈለግ ወይም ያገኙትን ስራ በአግባቡ መያዝ

# አገር አቀፍ የአካል ጉዳተኝነት የመድህን ዋስትና አሰራር (NDIS) የገንዘብ እርዳታ የማያደርግበት ሁነታዎች

ከዚህ ለሚከተለው ለማኝኛውም ነገር አገር አቀፍ የአካል ጉዳተኝነት የመድህን ዋስትና አሰራር (NDIS) የገንዘብ እርዳታ አይሰጥም፡

- ከግለሰቡ የአካል ጉዳተኝነት ጋር ግኑኝነት ለሌው ጉዳይ
- ለግለሰቡ የእለት ተእለት ኑሮ አስፈላጊ ወጪዎች ነገር ግን ከአካል ጉዳተኝነት ድጋፍ ጋር የማይገናኙ ከሆነ
- ከሌላ ድርጅት የገንዘብ እርዳታ የሚያገኙ ከሆነ - ለምሳሌ ከትምህርት ተቋም፣ ከጤና ወይም ከመኖሪያ ቤት አገልግሎቶች
- በተሳታፊው ወይም በሌሎች ሰዎች ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችልበት ሁነታ ካለ።



# የአካል ጉዳት ያለባቸው ህጻናት

አገር አቀፍ የአካል ጉዳተኝነት የመድህን ዋስትና አሰራር (NDIS) የአካል ጉዳት ላለባቸ ህጻናት በጊዜ ድጋፍ እንዲያገኙ መርዳት ይችላል። በጊዜ ድጋፍ ማግኘት በርስዎ ወይም በልጅዎ ላይ ለረጅም ጊዜ በሚቆይ የአካል ጉዳኝነት ምክንያት ሊከሰቲ የሚችሉ ችግሮችን ለመቀነስ ሊረዳ ይችላል። አገር አቀፍ የአካል ጉዳተኝነት የመድህን ዋስትና አሰራር (NDIS) ይህን "በጊዜ ጣልቃ መግባት/ early intervention" በሚል ይጠራዋል።

# የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች እና ቤተሰብ

ምርጫ ና ውሳነን ጨምሮ የአካል ጉዳት ያለባቸዉ ሰዎች ፍላጎቶች፤ አገር አቀፍ የአካል ጉዳተኝነት የመድህን ዋስትና አሰራር (NDIS) እነሱን ለመርዳት በሚያወጣው እቅድ ውስጥ ቁልፍ ቢሆኑም አካል ጉዳት ያለባቸዉ ሰዎች ቤተሰቦች ሚናም አስፈላጊ ነው።

የአካል ጉዳት ያለባቸዉ ሰዎች የአገር አቀፍ የአካል ጉዳተኝነት የመድህን ዋስትና አሰራር (NDIS) እቅድ ማውጣት ሂደት ጋር በተያያዘ እንዲረዷቸው ቤተሰቦቻቸውንና ሌላ ድጋፍ ሊያደርጉላቸው የሚችሉ ሰዎችን መጋበዝ ይችላሉ። ቤተሰብ ተከታታይ የሆነ ድጋፍ እንዲያደርግ የአገር አቀፍ የአካል ጉዳተኝነት የመድህን ዋስትና አሰራር (NDIS) እቅድ አውጪዎች መንገድ በማመቻቸት ይረዳሉ፤ ከተሳታፊዎች ጋር ሆነው እቅድ በሚያወጡበት ጊዜ እቅድ አውጪዎቹ የቤተሰብ ሚና ግምት ውስጥ ያስገባሉ፤ ይህም ቤተሰብ የሚሰጡት ድጋፍ፣ ሌላ ሃላፊነቶች፤ እና የራሳቸውን የህይወት ኑሮ እቅድን ያካተተ ይሆናል። እንዲሁም የአካል ጉዳት ያለባቸዉ ሰዎች በመረጃ የተደገፈ ውሳኔዎችን ለማድረግ እንድረዳቸው የቤተሰባቸውን ሃሳብ፣ እውቀትና ልምድ ሊፈልጉ እንደሚችሉ የአገር አቀፍ የአካል ጉዳተኝነት የመድህን ዋስትና አሰራር (NDIS) እቅድ አውጪዎች ግምት ውስጥ ያስገቡታል።

# አስተርጓሚ ካስፈለግዎት

ጥያቄ ለማቅረብ ወይም የበለጠ ለማወቅ አስተርጓሚ ከፈለጉ TIS በቁጥር 131 450 በመደወል ከአገር አቀፍ የአካል ጉዳተኝነት መድህን ዋስትና አሰራር/National Disability Insurance Scheme ጋር በስልክ ቁጥር 1800 800 110 እንዲያነጋግርዎ መጠየቅ ይችላሉ።

# አገር አቀፍ የአካል ጉዳተኝነት የመድህን ዋስትና አሰራር መስፈሪት እንደሚያማሉ እንዴት ማወቅ ይችላሉ?

ከሚከተለው ድሕረ-ገጽ ላይ አገር አቀፍ የአካል ጉዳተኝነት የመድህን ዋስትና አሰራር እርዳታ ለማግኘት የሚያስችል መስፈሪት እንደሚያማሉ ማረጋገጥ ይችላሉ።

http://www.ndis.gov.au/ndis-access-checklist

በኲዊንስላንድ ውስጥ አገር አቀፍ የአካል ጉዳተኝነት የመድህን ዋስትና አሰራር (NDIS) ሲጀምር፤ የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች "አገልግሎት መጠየቂያ ቅጽን" መሙላት ይችላሉ። ቅጹ አገር አቀፍ የአካል ጉዳተኝነት የመድህን ዋስትና አሰራር ድጋፍ ማግኘት መቻልና አለመቻልን ለመወሰን የሚያስችል መረጃ ይሰጣል። በቅጹ ላይ አካል ጉዳቶዎን፤ እድሜዎንና በአውስትራሊያ ውስጥ የርስዎን ዜግነት/መኖሪያ ፈቃድ ማቅረብ ይኖርብዎታል። የርስዎን አገልግሎት የማግኘት ጥያቄ በማስረጃ ለመደገፍ የሚያስፈልግ ቅጽ ና የመረጃ ዓይነት እና ሰነዶች (ለምሳሌ፡ *የአካል ጉዳተኝነት ማስረጃ፣ የመኖሪያ ፈቃድ፣ ኢድሜ ወዘተ*.) አገር አቀፍ የአካል ጉዳተኝነት የመድህን ዋስትና አሰራር (NDIS) ድረገጽ ላይ (በተሳታፊ/Participant ክፍል ስር) ቀርቧል።

# እቅድ ስለማውጣት

ሰዎች እንዴት ህይወታቸውን መምራት እንደሚችሉና ይህን ለማድረግ ምን ዓይነት እርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው ከአሁን ማሰብ ሊጀምሩ እና እቅድ ማውጣት ይችላሉ። ሰዎች ለእቅድ ማውጣት ዝግጅት ሂደት እንዲዘጋጁ እንዲረዳቸው የአገር አቀፍ የአካል ጉዳተኝነት የመድህን ዋስትና አሰራር (NDIS) እቅድ ማውጫ ሥራ መመዝገብያ ደብተር መሙላት ይችላሉ። የሥራ መመዝገቢያ ደብተር ቅጂው በአገር አቀፍ የአካል ጉዳተኝነት የመድህን ዋስትና አሰራር (NDIS) ድረገጽ ላይ ቀርቧል። የሥራ መመዝገቢያ ደብተር በሚከተሉት ቋንቋዎች ተተርጉሟል - ስፓኒሽ/Spanish, ቬትናመስ/Vietnamese, አረብኛ/Arabic, ግሪክ/Greek, ጣሊያን/Italian, እና የተሻሻለና ባህላዊ ቻይኒስ/Chinese ናቸው።

# ከአገር አቀፍ የአካል ጉዳተኝነት የመድህን ዋስትና አሰራር እቅድ አውጪ ጋር ስለመሥራት

አገር አቀፍ የአካል ጉዳተኝነት የመድህን ዋስትና አሰራር እርዳታ ለማግኘት መስፈሪት ማማላቶን በሚያውቁበት ጊዜ አገር አቀፍ የአካል ጉዳተኝነት የመድህን ዋስትና አሰራር የእቅድ ማዘጋጃ ጥሪዝ ይላከሎዎታል። ጥሪዙ ስለ እቅድ ማውጣትና ስለ ግምገማ አሰራር ይገለጻል፤ እንዲሁም ጥሪዙ ከእቅድና ከግምገማ አሰራር ሂደት በፊት መጠናቀቅ ያለበት የተሳታፊ ቃል ያካተተ ይሆናል። ሰዎች እርዳታ ከፈለጉ ማለትም አስተርጓሚ ወይም የተተረጎሙ ጹሁፎችን ከፈለጉ አገር አቀፍ የአካል ጉዳተኝነት የመድህን ዋስትና አሰራር (NDIS) ሊያግዞዎት ይችላል። እንዲሁም ለእቅድ ማዘጋጃ ስብሰባዎች የሚሆኑ የተተረጎሙ ጽሁፎችን ከፈለጉ መጠየቅ ይችላሉ።

የርስዎን አገር አቀፍ የአካል ጉዳተኝነት የመድህን ዋስትና አሰራር (NDIS) እቅድ ለማዉጣት አገር አቀፍ የአካል ጉዳተኝነት የመድህን ዋስትና አሰራር እቅድ አውጪ ጋር ስብሰባ ማድረግን ጨምሮ የተለያዩ መንገዶች ይኖራሉ። አገር አቀፍ የአካል ጉዳተኝነት የመድህን ዋስትና አሰራር (NDIS) ስለርስዎ ፍላጎቶች፣ ዓላማዎችና ምኞቶች እና በአሁኑ ጊዜ ስለሚያገኙት ድጋፎች ለመወያየት ይረዳል። ይህ ውይይት ከአንድ ጊዜ በላይ ሊያስፈልግ ስለሚችል እርስዎን የሚረዳ ለላ ሰው ይዘው መምጣት ይችላሉ። በውይይት ወቅት የተገኘውን መረጃ በመጠቀም አገር አቀፍ የአካል ጉዳተኝነት የመድህን ዋስትና አሰራር (NDIS) ፍላጎቶን እና ዓላማዎን የሚያማላ የእርዳታና ድጋፍ እቅድ ያወጣል። እቅድ በሚወጣበት ጊዜ ሌሎች ሰዎች ድጋፍና እርዳታ እንዲሰጡ መጋበዝ ይችላሉ።

ለበለጠ መረጃ ድረገጽ www.ndis.gov.au

***ይህ መረጃ የተዘጋጀው በAMPARO Advocacy Inc. ነው***

ይህ መረጃ ተዘጋጅቶ ስታተም በጊዜው ትክክለኛ መረጃ መሆኑን ለማረጋገጥ መደረግ ያለበት ጥንቃቀ ሁሉ ተደርጉዋል። ይህ ዝርዝር መረጃ ግቡ አጠቃላይ መግለጫ ለመስጠት ተብሎ የቀረበ ሲሆን አሁን ባለበት ሁኔታ ትክክለኛ፣ ወቅታዊ ወይም የተጠናቀቀ ላይሆን ይችላል። በበለጠ በግልዎ ምክር ቢያገኙ በጣም ይመረጣል።

Date: August 2015

AMPARO Advocacy inc
9 Chippendall St, Milton QLD 4064
info@amparo.org.au, www.amparo.org.au
phone 07 3369 2500
Interpreter Service 13 14 50